የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

(ሚያዝያ 28 ግንቦት 5/2016 ዓ.ም)
May 13-21/2024

## በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

**1. ባለፉት ዘጠኝ ወራት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም በበጀት ዓመቱ ለማሳካት የታቀደውን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ እንደሚቻል ያመላከተ ነው-ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር)**

የባለፉት ዘጠኝ ወራት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም በበጀት ዓመቱ ለማስመዝገብ የታቀደውን የ7 ነጥብ 9 ኢኮኖሚያዊ እድገት ማሳካት እንደሚቻል ያመላከተ መሆኑን የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር) ገለጹ። የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍፁም አሰፋ፤ ሀገራዊ የዘጠኝ ወራት የልማት አፈፃፀምን በተመለከተ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ሰጥተዋል።

**ኢዜአ፡ ግንቦት 12/2016**

በመግለጫቸውም በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በመሠረተ ልማትና በፕሮጀክቶች፣ በሪፎርም ሥራዎች እንዲሁም በሌሎች አበይት ጉዳዮች ላይ የተመዘገቡ ውጤቶችን ዘርዝረዋል። ይህንንም ተከትሎ በግ**ብርና ዘርፍ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ዋና ዋና ከሚባሉ** ሰብሎች ከ100 ሚሊየን በላይ ኩንታል ምርት መሰብሰቡን ጠቅሰው ከ6 ነጥብ 58 ሚሊየን ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ መሸፈኑን ተናግረዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_4459587

**2. አማዞንን ጨምሮ ጉግልና አፕል የተጨማሪ ዕሴት ታክስ እንዲመዘገቡ የሚያስገድድ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጀ**

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለፈው ሳምንት የተመለከተውና ለዝርዝር ዕይታ ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመራው የተጨማሪ እሴት ታክስ ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ፣ እንደ የሌሎችን ምርቶች ለገበያ የሚያቀርቡ የውጭ ኩባንያዎች እንደ ጉግል ፕሌይና አፕል ስቶር በመሳሰሉ ሥርዓቶች አማካይነት ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያከናውኑት ግብይት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ መመዝገብ እንዳለባቸው ይደነግጋል።

**ሪፖርተር፡ May 19, 2024**

በረቂቅ አዋጁ እንደተመለከተው፣ ኩባንያዎቹ በኢትዮጵያ የባንክ ሒሳብ መክፈት አለባቸው፡፡ ባንክም ከሒሳባቸው ላይ ታክሱን ቀንሶ ያስቀራል፡፡ ኩባንያዎቹ በማናቸውም ምክንያት ያልተመዘገቡ ከሆነ፣ በየዓመቱ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት የሚያገኝ ለታክሱ ያልተመዘገበ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው መመዝገብ፣ ታክሱን ራሱ ከሚከፈለው ገንዘብ ላይ በማስላት መክፈል እንዳለበት የሚደነግጉ አንቀጾች በረቂቁ ተካተዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129633/

**3. የታሸጉ መጠጦችና የፍራፍሬ ጭማቂ አምራቾች በኤክሳይዝ ታክስና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ቅሬታ አቀረቡ**

የታሸጉ መጠጦችና የፍራፍሬ ጭማቂዎችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ዘርፈ ብዙ ችግሮች ውስጥ እየገቡ መሆኑን እየገለጹ ነው፡፡ የኢትዮጵያ በቨሬጅስ አምራቾች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር ባለፈው ሐሙስ ባካሄደው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ እንደተደመጠው በተለይ የታሸጉ ውኃዎች አምራቾችና የአትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ሥራቸውን ለማስቀጠል የሚያስችሉ የተለያዩ ተግዳሮቶች እየገጠማቸው ነው፡፡

**ሪፖርተር፡ May 19, 2024**

በአሁኑ ወቅት እየገጠሙ ያሉት ችግሮች በርካታ ናቸው ያሉት የማኅበሩ አባላት እየገጠሙን ላሉ ተግዳሮቶች መፍትሔ እየተገኘላቸው ባለመሆኑ ፋብሪካ እስከመዝጋት እየተደረሰ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው አትክልትና ፍራፍሬዎችን የሚያቀነባብሩ 16 ፋብሪካዎች ከሥራ ውጭ መሆናቸውን ለአብነት ገልጸዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129679/

**4. በአዲስ አበባ ለሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጡ ድጋፎችንና መሥፈርቶችን ያካተተ አዲስ መመሪያ ወጣ**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማው ወስጥ ለሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች የቦታና የብድር አቅርቦት ጨምሮ ሌሎች ልዩ ልዩ ድጋፎችን የሚያቀርብበት አዲስ መመሪያ በማውጣት ወደ ትግበራ ሊገባ መሆኑን አስታወቀ። ‹‹የአምራች ኢንዱስትሪዎች ልማት የአገልግሎትና ድጋፍ ማዕቀፍ›› በሚል ርዕስ የወጣው አዲስ መመሪያ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ከዚህ በኋላ ተፈጻሚ ሊያደርጋቸውና ሊደረግላቸው የሚገቡ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡

**ሪፖርተር፡ May 15, 2024**

መመርያው ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጡት የመሥሪያ ቦታዎች በምን አግባብና ምዘና እንደሚሰጡም የሚያመላክት ነው፡፡ ቦታ ተጠቃሚ አምራች ኢንዱስትሪዎች ልየታና ምልመላ በማድረግ የሚተገበር ሲሆን፣ የተጠቃሚዎች ልየታና ምልመላን በተመለከተም ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዟል።

**https://www.ethiopianreporter.com/129594/**

**5. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተግዳሮቶች፣ መውጫዎችና መልካም እድሎች**

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በኢትዮጵያ የልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ልዩ ሚና እንዳለው ይታመናል። ዘርፉ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች እንዲካሄዱ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ሥራዎች እንዲሳኩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ይታወቃል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ከሀገሪቱ የካፒታል በጀት 60 በመቶውን የሚጠቀም ግዙፍ ዘርፍ ነው። ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት 23 ነጥብ 2 በመቶውንም ይሸፍናል። በቀጥታና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሥራ እድል በመፍጠር በኩልም ከግብርናው ዘርፍ ቀጥሎ ይጠቀሳል።

**ኢትዮጵያ ፕረስ ኤጀንሲ፡ May 18, 2024**

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማና መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በቅርቡ ‹‹የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተግዳሮት፣ መውጫ መንገዶችና የሕግ አውጪው ሚና›› በሚል በምክር ቤቱ አዳራሽ ባዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ በቀረቡ ጽሑፎችም ሆነ በተሰጡ አስተያየቶች እነዚሁ ችግሮች ተጠቁመዋል

**https://press.et/?p=128069**

**6. የፕላስቲክ አምራቾች የወረቀትና የጨርቅ ከረጢቶችን በአፋጣኝ ማምረት እንዲጀምሩ ማሳሰቢያ ተሰጠ**

ከ0.03 ማይክሮ ሜትር በታች የሆነ ፕላስቲክ ከረጢት የሚያመርቱ እስከ አሥር ዓመታት ይታሰራሉ

አካባቢን ሊበክሉ የሚችሉ ስስ ፕላስቲኮችን የሚያመርቱ ድርጅቶች የአካባቢ ብክለትን የሚቀንሱ የወረቀትና የጨርቅ ከረጢቶች በአፋጣኝ ማምረት እንዲጀምሩ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አሳሰበ፡፡

**ሪፖርተር፡ May 15, 2024**

ፕላስቲክ በማምረት የተሰማሩ ድርጅቶችና ባለቤቶች ከተፈቀደላቸው 0.03 ማይክሮ ሜትር በታች ሲያመርቱ ከተገኙ፣ ከመዝጋታቸው ባሻገር፣ ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት የእስር ቅጣት እንደሚያስከትልባቸው ተገልጿል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129523/

### 7. ኢትዮጵያ በአኅጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና ጠንካራ ተሳትፎ ለማድረግ እየተዘጋጀች ነው

ኢትዮጵያ በአፍሪካ አኅጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና ጠንካራ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝግጅቶችን እያደረገች መሆኗን የጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ። ከአኅጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ጋር በተገናኘ የጉሙሩክ እንቅስቃሴን ለማሳለጥ ዘመናዊ አሠራር እየተዘረጋ መሆኑን በኮሚሽኑ የታሪፍና ስሪት አገር ዳይሬክተር ካሳዬ አየለ ገልጸዋል።

**ፋና፡ ግንቦት 11፤ 2016**

ለአብነትም የድንበር አሥተዳደርና የካርጎ ፍተሻን ኤሌክትሮኒክ ማድረግን ጨምሮ በድሮን የታገዘ የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን ጠቅሰዋል።
በነጻ የንግድ ቀጣናው የዚህ አሠራር ተግባራዊ መሆን ደግሞ በዕቃዎች መተላለፍና ግብይት ወቅት በቀላሉ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ የሚያስችል መሆኑን ለኢዜአ ተናግረዋል።

https://www.fanabc.com/archives/246620

## *በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች*

### 9. Nyala Insurance launches life insurance coverage for workers traveling abroad

Nyala Insurance S.C. (NISCO) has announced the Commencement of insurance coverage for more than half a Million workers traveling abroad. With their strong financial Resources and commitment to innovative insurance solutions, Nyala has launched life insurance services specifically tailored for Ethiopian citizens seeking employment opportunities overseas.

**Capital Ethiopia: May 20, 2024**

Through a two-year contract secured with the Ministry of Works and Skills, NISCO is now able to provide life insurance coverage to over 500,000 Ethiopians traveling abroad for job opportunities. The coverage offers a maximum benefit of 1.35 million birr per individual, with an annual premium of 500 birr.

https://www.capitalethiopia.com/2024/05/20/nyala-insurance-launches-life-insurance-coverage-for-workers-traveling-abroad/

### 10. The United Nations on Thursday reported improved prospects for the world economy since its last forecast in January.

Its mid-2024 report points to a better outlook in the United States and several large emerging economies, including Brazil, India, and Russia.
According to the report, the world economy is now projected to grow by 2.7 per cent this year, up from the 2.4 per cent it forecast in its January report – and by 2.8 per cent in 2025.

**Africa news: May17, 2024**

Our prognosis is one of guarded optimism, but with important caveats," said Shantanu Mukherjee, the director of the UN's Economic Analysis and Policy Division, at a news conference launching the report.

**https://www.africanews.com/2024/05/17/un-forecasts-improved-prospects-for-the-world-economy/**

### 11. Oil prices increase following Iranian president's tragic death

Oil prices spiked on Monday after Tehran confirmed the deaths of Iranian President Ebrahim Raisi, Foreign Minister Hossein Amir-Abdollahian, and other officials in a helicopter crash in the country's northwestern province.
International benchmark Brent crude traded at $84.24 per barrel at 10.44 a.m. local time (0744 GMT), a rise of 0.31% from the closing price of $83.98 per barrel in the previous trading session.

**Anadolu: May 20, 2024**

American benchmark West Texas Intermediate (WTI) traded at $79.81 per barrel at the same time, a 0.29% increase from the previous session that closed at $79.58 per barrel.
The helicopter carrying the Iranian president, the country's foreign minister, and their entourage crashed in the East Azerbaijan region of northwest Iran on Sunday afternoon.

**https://www.aa.com.tr/en/economy/oil-prices-increase-following-iranian-presidents-tragic-death/3224630**

### 12. Gulf States intensify scramble for control of Africa investments

The African investment landscape faces a major shift as Gulf Co-operation Council (GCC) member States — especially Saudi Arabia, the United Arab Emirates (UAE) and Qatar — increase their footprint on the continent, largely under the control of the Chinese investors.

**The east African: May 19, 2024**

A new report by the Economist Intelligence Unit (EIU), the research and analysis division of The Economist Group, shows that GCC companies and institutions are targeting a larger share of Africa's resource industries of oil and gas, mining and agriculture, while consolidating their strong position in transport infrastructure and logistics services, and expanding into renewable energy, digital infrastructure, manufacturing ventures and financial services.

**https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/gulf-states-intensify-scramble-for-control-of-africa-4627042**

### 13. Safaricom eyes $150m debt in Ethiopia money

Safaricom PLC will be looking to rise up to $150 million (Ksh19.6 billion) over several years in local currency debt in Ethiopia once the country's securities exchange goes live in the third quarter of 2024.

**The east African: May 21, 2024**

This means that at the present exchange rate, Safaricom PLC plans to raise as much as 8.6 billion Ethiopian Birr through the issuance of local currency-denominated bonds any time starting September.

**https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/safaricom-eyes-150m-debt-in-ethiopia-money-4629900**